# ሁለተኛው አፊዴቪት በአንጃዎች ቤት ሲሰለቅ

ከቤልጅግ አሊ

ይህንን ፅሁፌን ስታነቡ በቀጥታ አንጃ ብዬ ስፅፍ ከኢ.ሕአፓ የወጡትን ግለሰቦች በሞላ ሳይሆን በቀንደኝነት በመቆም የተነሱበትን አላማ ሽጉጠው በኢ.ሕአፓ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥፋት ለማድረስ የተነሱትን መሰሪዎችን ማለቴ መሆኑን እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ።

አፊዴቪት የሚለው ቃል አሁን በቅርብ ግዜ በሁሉም ቦታ ተነስቶ ውይይት ሲደረግበት የነበረና አሁንም ወደፊትም ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ እየተደጋገመ የሚነሳ ይሆናል። አፊዴቪት ወያኔ ኢ.ሕአፓን እግር ከወርች ለማሰር ያቀረበውና አንዳንድ በተለያየ ምክንያት ትግሉን ማህል ላይ ለማቆም የከጀሉ ደካማ ግለሰቦችን የአቋም ጥንካሬ የሰለበበት የመርዝ ብልቃጥ ነው። አፊዴቪት እንደ ኢ.ሕአፓ አይነት ለሆኑ ድርጅቶች በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ከፈለጉ በወያኔ እንዲፈርሙ የቀረበላቸው ሰነድ ሲሆን፣ በኢ.ሕአፓ ውስጥ ውይይት ተደርጎበት በአብዛኛው ተቃውሞ የወደቀ ነበር። የኢ.ሕአፓ ሚስጥር ከድርጅቱ በወጡ አንጃዎች ሲዝረከረክ ይህንን ያልሰማ እንደማይኖር እርግጠኛ መሆን ይቻላል።

የአፊዴቪትን ጉዳይ በጉጉት ይጠባበቁ የነበሩና ከዛ በሚገኘው ጥቅም ምክንያት ምራቃቸው ይዝረበረብ የነበር፣ የትም ፍጭው ገንዘቡንና ስልጣኑን አምጭው በሚሉ በተለይም በድርጅቱ ውስጥ ተሰሚነት አለን የሚሉ ግለሰቦች ይህንን የብዙሃኑን ድምፅ እንደስድብ መቁጠራቸው አልቀረም። አንዳንዶቹ አልፈው ተርፈው እኔ ያልኩት ካልሆነ ድርጅቱ ይፈርሳል ብለው አደባባይ መናገር መጀመራቸው ለኢ.ሕአፓ አባላት ምንም ድብቅነት አልነበረውም።

እነዚህ ግለሰቦች በድርጅቱ ውስጥ በተለያ መንገድ አባላቶቻቸውን በድብቅ ሲመለምሉ እንደነበር እውቅ ነው። የተጠቀሙበት መንገድ ደግሞ አስነዋሪና አሳዛኝም ጭምር ነው። ለምሳሌ በግል ለመታወቅ የሚፈልጉትን፣ በዘር በቄዬ የሚያምኑትን ፣ ልዩ ልዩ ደካማ ባህሪያቸውን በመጠቀም ደጋፊዎቻቸውን ለማሰባሰብ ተጠቅመዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለድርጅቱ እድገት በጣም የሚቆረቆሩትን በማወናበድ በኢ.ሕአፓ ውስጥ አለ ለሚባለው ድክመት በሙሉ ተጠያቂዎቹ ሌሎች ናቸው እኛ አደለንም በማለት አባላትን በመከፋፈልና የሃሰት ወሬዎችን በመንዛት እውነተኛ የሆኑ የኢ.ሕአፓ አባትን ስውር አላማቸውን ደብቀው ለማወናበድ ችለዋል።

በድርጅቱ ውስጥ ቡድን ማቀቋም የግል ጥቅማቸውን፣ ተዋቂነታቸውንና አንዳንድ ተልካሻ ፍላጎታቸውን ለማሟላት መራወጥ መጀመራቸው ሲታወቅ በውስጥ በተደረገው ትግል ይህ የተቋቋመው ቡድን መፍረስ አለበት በማለት ትልቅ ትግል ተካሂዷል። ይህ በሆነ ግዜ እነዚህ የአፊዴቢት ተስፈኞች ከአውሮፓ ሳይቀር በመፍለስ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመክተም የድሮ የኢ.ሕአፓ አባላትን ማሰባሰብ በሚል ስም ድርጅቱን ለማፍረስ ቀን ከሌሊት መስራት መጀመራቸውም እውቅ ነው። ታዲያ ይህ መሰሪ ተግባራቸውን በውስጣቸው አምቀው እንደተበደሉ የአዞ እንባ እያነቡ አንዳንድ የዋሆችን ለማሳሳት የሞከሩት ሙከራም በከፊል ተሳክቶላቸዋል።

የኢ.ሕአፓን አስቸኳይ ጉባኤ ረግጠው በሚወጡበት ግዜ አፊዴቪት ከጉባኤው የወጣንበት ምክንያታችን አደለም፣ ነገር ግን የወጣንበት ምክንያት ሁለት አምባገነኖች ስላስቸገሩን ነው ብለው ገልፀውም ነበር። ከወጡ በሁዋላ የሚያሳዩት አቋም አፊዴቪት አሁንም በውስጥ ልባቸው ውስጥ ተፅፎ የቀረ መሆኑን ነው። ዛሬ በሚያወጡዋቸው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መግለጫዎች ውስጥ የሚንፀባረቀውን ላስተዋለ በሙሉ በኢሕአፓ አባላት በድምፅ የወደቀው የአፊዴቢት ጥያቄ ቁርሾ ምን ያህል የመፈርጠጫ ምክንያታቸው መሆኑን ለመረዳት አያዳግተውም።

ስሞኑን በተበተነው ጉደኛ ፅሁፍ ላይ በግንቦቱ ምርጫ ለመሳተፍ የተጠየቀውን አፊዴቪት ላለመቀበል የተደረገው የብዙሃን ውሳኔ ቀኖናዊነት ነው በማለት የተጠቀሰውን ስመለከተው የዚህ ቡድን መሪዎች አብረዋቸው ካሉት አባለት የተለየ ፍላጎት እንዳላቸው ግልፅ ያደርግልናል። አሁን ጥርት እያለ የመጣውን የነመርሻንና የእነ ጌታቸውን የተደበቀ አቋም እውነትና ንጋት እያደረ ነው እንዲሉ ዛሬ በመርዝ የተለወሰውን የድብቅ ስምምነት በሰሞኑ መግለጫቸው ውስጥ በተዝረከረከ መንገድ ሲያቀርቡት ስመለከት አብሬያቸው ስንት ሰቃይ የተቀበልኩት የቀድሞ ጓዶቼ ከዚህ የበለጠ ክብር ይገባቸዋል እንጂ አንዴ ከኢሕአፓ ወጥተዋል ተብለው በንቀት ብቻ ብዙሃኑ የማይደግፉትን መግለጫና ተግባር ማድረግ ምንኛ አስነዋሪ ነው።

እስቲ እያንዳነድዱን እንመልከት በፅሁፉ በገፅ 3 ላይ እንዲህ ይላል፦

«በፓርላማ መቀመጫ የተሰጣቸውን ተቃዋሚዎች ደበልጥ ስንመረምር ደግሞ በሁለት ክፍለን ፊናያቸው እንገደዳለን፡፡ አንደኛው ወገን የግልን ጥቅም በአድርባይነት በማሳደድ አገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ስለ መዷዟ ደንታ የሌለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አገሩን ከልብ የሚወድ ነገር ግን ፓርላማውን ጥሎ ቢወጣና በተከታታይ በምርጫ ካልተሳተፈ በህወሓት ሕገ መንግስት መሰረት “ህጋዊነቱን” ማጣቱ አስጨንቆት ተቀፍድዶ የተያዘ ነው፡፡»

ይህ እውን ነው? ፓርላማ ከገቡት ውስጥ ሃገሩን በጣም የሚወደው ማነው? በየነ ነው ወይስ ልደቱ? በመንገድ ላይ በተራራ ጸሃይ እነዚያ ወጣቶች ሲረሸኑ ፓርላማ መግባትና ህጋዊነትን መከላከል የመጨረሻው አላማቸው ስለሆነ ነው አንጃዋቹ የሚደግፏቸው? መልሱን ከአንጃ መሪዎች እጠብቃለሁ። ይህ ለምን እንዲህ እንደተፃፈ ይታወቃል። ሊበሉዋት ያሰቡዋትን ጅግራ ቆቅ ነች ይሏታል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ የሚቀጥለው ነው።

«በሌላ በኩል ሃቀኛ ተቃዋሚ ሃይሎች ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በጅምላ ማውገዝ ሳይሆን ሐቀኛውን ክፍል መለየትና ከሱም ጋር የትግል አንድነት ለመፍጠር መቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ካለፈ ስህተት ትምሕርት ይሆነን ዘንድ እዚህ ላይ አንድን አመለካከት ለመጥቀስ እንወዳለን፡፡ አንድ የተቃዋሚ ክፍል በፖለቲካ ቀኖና ተቀፍድዶ ተይዞ ተቃዋሚ ድርጅቶች በምርጫ 97 ተሳትፎ እንዳያደርጉ ቀስቅሶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ምርጫው ግንቦት ላይ ሊካሄድ ይህ በቀኖናዊ ፖለቲካ የተቀፈደደ ክፍል የካቲት ላይ ባወጣው መግለጫው ላይ “መጭው የወያኔ ምርጫ (ግንቦት 1997 ማለቱ ነው) ነፃና ፍትሃዊ እንደማይሆንና የተቃዋሚ ድርጅቶችም በዚህ ምርጫ ለወያኔ ሽፋን ሰጭ መሆን እንደሌለባቸው ህዝቡ በሚገባ አስረግጦ ነግሮዋቸዋል፡፡...ይልቁንም ህብረታቸውን አጠንክረው ትግሉን በመምራት ለድል እንዲያበቁት በአፅንቅስት አሳስቧቸዋል፡፡” ብሎ ጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ ይህ ቀኖናዊ አመለካከት ስለ ምን ዓይነት ትግል እንደሚያወራ በትክክል ግልፅ አልነበረም፡፡ በምርጫ 97 ዙሪያም የተደረገው ትግል በኢትዮጵያ ታሪክ አኩሪ እንጂ ይኸው ቀኖናዊ አመለካከት እንደሰበከው ለአገዛዙ ሽፋን መስጠትን ዓላማው አድርጎ አልተንቀሳቀሰም፡፡ ምርጫው ባይደረግ ኖሮ ወይም ቡድኑ እንደተመኘው ተቃዋሚዎቹ በምርጫው ባይሳተፉ ኖሮ ክስረት ከመከተሉም በላይ የህወሓት አውሬያዊ ገጽታ ባልተጋለጠም ነበር፡፡»

ይህንን ከላይ ያለውን ፅሁፍ ለተመለከተ አፊዴቪት የሁሉም ችግሮች መንስኤ መሆኑን ለማወቅ አይቸግረውም። ቀኖናዊነት የተባለው እንግዲህ ምን እንደሆነ ድብቅ አደለም።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከዚህ በላይ ለተፃፈው መልሱ አደባባይ ላይ ሰለሆነ መልስም አያስፈልገውም። ለነገሩማ መልሱን እነርሱ አጥተውት ነው።

በዚህ መግለጫቸው ላይ በገጽ 5 ያለውን እንመልከት

« ዛሬምእንደገና የሕዝብ ድምፅ እንዲሰረቅ ምክንያት የሆኑት የተቋም ለውጦች ሳይደረጉ አገራዊ ምርጫን ድጋሚ ማሰብ፤ ምርጫ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አሸጋጋሪ ሳዳና መሆኑን መዘንጋት ይሆናል። ነፃ ምርጫን ለማከናወን ከሁሉም ፓርቲዎች ወኪሎች የተውጣጣ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ወይም ከማንም ፓርቲ ያልወገኑ ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ ዝርዝራቸውም በፖለቲካ ፓርቲዎችና በመንግስት ስምምነት የሚፀድቅ የምርጫ ቦርድ ካልተዋቀረ በስተቀር አሁን ባለው መልኩ በድጋሚ የሚደረግ አገራዊ ምርጫ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ አይወስድም።»

የኔ ጥያቄ እዚህ ላይ ሊሆን የሚችለው የአንጃው መሪዎች በገፅ 4 እና በገጽ አምስት ላይ የተፃፈውን አስማምተው እንዲያስረዱን ነው። አለበለዚያ ግን ቀኖናነት ምን ማለት እንደሆን ሊያስረዱን ይገባል።

እኔ በግሌ አሁንም ቢሆን ተሳፋ ያልቆረጥኩበት ጉዳይ ቢኖር በአንዳንድ ተልካሻ ምክንያት ከኢሕአፓ የወጡት አባላት ተመልሰው ድርጅታቸውን እንዲያጠናክሩ በኢሕአፓ በኩል ከፍተኛ ጥረት እንደሚስፈልግ ነው።

አንጃው ክፍል ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ የቅርብ የቀድሞ ጓዶቻችንን ልጠይቃቸው የምፈልገው ቢኖር:

1ኛ. ከጉባኤው የወጣችሁት ለኢሕአፓ ታሪክም ሆነ ለፓርቲው ህልውና ጠላት ለሆኑ ተሽናፊ ሆናችሁ በየፓልቶኩ እየሄዳችሁ ይቅርታ ለመጠየቅ ነው?

2ኛ. የስዬ አብርሃም ስብሰባ ቀስቃሽ ሆናችሁ የጓዳችሁን የፀጋዬን ሁኔታ ለመጠየቅ ነው?

3ኛ . አፊዴቪት አሁን እንደገና ተፈርሞ ለወያኔ ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆን ነው?

4ኛ. እንደዚህ ግራ የሚገባ መግለጫ በስማችሁ እየወጣ ግለሰቦች በእናንተ ማንነት ላይ የግል ጥቅማቸውን ማሳደጃ ለመሆን ነው?

5ኛ. የተሰው ጓዶቻችሁን ታሪክ ለማጥፋት ከሚጥሩ፣ እናንተ ቀድሞ ትዋጓቸው ከነበሩት ስር ለድጋፍ ስትሉ ለመለማመጥ ነው?

አንዳንዶቻችን ከጉባኤው ጥላችሁ ስትወጡ የተሰማንን ሃዘን ልትገምቱት የምትችሉም አትመስሉኝም። በእልክ ፈረስ ላይ ተሳፍራችሁ ለማታምኑበት አላማ ቆማችሁ ለግለሰቦች መጠቀሚያነታችሁ እስከመቼ እንደሆነ ልታስቡት ይገባል። እኔ እግረ መንገዴን ይህንን አሁን ከላይ የጠቀስኩትን ልብ ብላችሁ አንብቡትና ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን መሞከርም ይኖርባችሁዋል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com